31ኛ ዓመት ቁጥር 204
አሶሳ፣

የካቲት/ 2017 ዓ.ም

ፖ.ሳ.ቁ. 293

ያንዱ ዋጋ----------

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

# ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

LISAN HIG-GAZETA

Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት**

**ጠባባቂነት የወጣ**

## አዋጅ ቁጥር 204/2017 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የባህል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና እውቅና ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ መስፈርቶችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግስት መሰረታዊና ሠብዓዊ መብቶችን፣ ዲሞክራሲን እና ሕገ-መንግስቱን የማይቃረኑ ባህሎች እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ ለመርዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፤

ጉዳያቸው በባህላዊ ሥርዓት መሠረት እንዲታይላቸው የሚፈልጉ ተከራካሪዎች የፌዴራልና የክልሉ ሕገ-መንግስት በሚፈቅደው መሠረት በሚቋቋሙና ዕውቅና በሚሰጣቸው የባህል ፍርድ ቤቶች መስተናገድ እንደሚችሉ የተደነገገ በመሆኑ፤

ማህብረሰቡ ተደራሽ የፍትህ አገልግሎትን እውነትን በማውጣትና ፍትህን በማስፈን ውጤታማ የሆኑ ቀለል ያለ ሥነ-ሥርዓትን የሚከተሉና ማህበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር ውጤታማ የሆኑ የባህል ፍርድ ቤቶችን ለማደራጀት የሚረዳ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ (3.1) መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ **"የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የባህል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና እውቅና ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ መርሆችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 204/2017 ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "**ሕገ-መንግስት**" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት ማለት ነው፤
2. **"ክልል"** ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማለት ነው፤
3. **"ባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 የተቋቋመ የክልል የባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት ማለት ነዉ፤
4. **"የባህል ሕግ"** ማለት የባህል ፍርድ ቤቱ የሚሰራበት አካባቢ የሚገኙ ብሄረሰቦች የባህል ሕግ ሆኖ ሕገ-መንግስትን ሞራልንና የተፈጥሮ ፍትሕን የማይቃረን ሕግ ማለት ነው፤
5. **"ፍርድ ቤት"** ማለት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት እና በክልሉ ፍርድ ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ፍርድ ቤት እንዲሁም የከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ማለት ነው፤
6. **"የባህል ፍርድ ቤት"** ማለት የባህል ሕግ ላይ ተመስርቶ እንዲሰራ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ወይም ዕውቅና የተሰጠው የህዝብ ተቋም ማለት ነው፤
7. "**የባህል ዳኝነት ችሎት**" ማለት የባህል ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን የሚያከናውኑበት ቦታ ማለት ነው፤

8. **“ሽማግሌ”** ማለት በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራትን እንዲያከናውን ተመርጦ በባህል ፍርድ ቤት የሚመደብ ሰው ሆኖ እንደ ክልሉ ብሄረሰቦች ባህልና አከባቢው የባህል ሕግ መሰረት በሌላ ስም ሊጠራ የሚችል ይሆናል፤
9. **“ኮሚቴ”** ማለት የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎችን ለማስመረጥ በወረዳ ፍርድ ቤት የሚቋቋም አካል ማለት ነው፤
10. **“ፀኃፊ”** ማለት የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎችን እንዲያግዝ እንዳስፈላጊነት የሚመደብ ባለሙያ ማለት ነው፤
11. **“አጥጋቢ ምክንያት”** ማለት የባህል ፍርድ ቤቱ የሚሰራበት አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ በባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች እንደ ምክንያት የሚወሰድ አሳማኝ ምክንያት ማለት ነው፤
12. **“ሰብሳቢ”** ማለት የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ሆኖ በዚህ አዋጅ ተጨማሪ ሥራዎች እና ኃላፊነቶች የተሰጠዉ ሰው ማለት ነው፤
13. **“ባለጉዳይ”** ማለት በባህላዊ ፍርድ ቤት ተከራካሪ፣ ባለጉዳይ፣ ተሽማጋይ፣ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ይግባኝ ባይ፣ መልስ ሰጪ የሆነ ሰው ማለት ነው፤
14. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ 3
## የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀዉ የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡

## አንቀጽ 4
## የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በክልሉ የሚቋቋሙ ወይም እውቅና የሚሰጣቸው ባህላዊ ፍርድ ቤቶች መሠረት ጉዳዩ እንዲታይለት ፈቃደኝነቱን በሰጠ ሰው ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በብሄረሰቦችና በአከባቢዉ ባህል መሰረት በባህል ፍርድ ቤት መፍትሄ እንዲሰጠዉ ያመለከተ ማንኛዉም ሰዉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የባህል ፍርድ ቤት ዓላማ፣ መርሆችና ጥበቃ

### አንቀጽ 5

### የባህል ፍርድ ቤት ዓላማ

የባህል ፍርድ ቤት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሲቋቋሙ፣ እውቅና ሲሰጣቸው ወይም ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሠብዓዊ መብቶች እና ዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎችን በማይጻረር እና ባከበረ መልኩ እንዲሆን አቅጣጫ የሚሰጡ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን ማስቀመጥ፤
2. የባህል ሕግ እና እሴቶቹን መሠረት አድርጎ አለመግባባትን እንዲፈታ ማድረግ፤
3. የባህል ሕግ ላይ የተመሠረተ እውነት እና ፍትህን በማስፈን ረገድ የተሻለ የባለጉዳዮች ማህበራዊ ግንኙነት ማጠናከር የሚችል የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓትን ሥራ ላይ በማዋል የዜጎች ሠብዓዊ መብቶችና የሕግ የበላይነት እንዲከበር አስተዋፅኦ ማድረግ፤
4. የክልሉ ማህበረሰብ ተደራሽ የሆነ ቀለል ያለ ሥነ-ሥርዓትን የሚከተልና ወጪው አነስተኛ የሆነን የፍትህ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ፤
5. የባለቤትነት ስሜት የተረጋገጠበትና ለክልሉ ብሄረሰቦች ባህል እሴትና ቋንቋ እድገት አስተዋፅኦ የሚያደርግ የሕግ እና የፍትህ ሥርዓት መፍጠር፤
6. ባህላዊ የሙግት መፍቻ እሴቶችና ሥርዓቶችን ለመጠበቅና ለማበረታታት፡፡

### አንቀጽ 6

### የባህል ፍርድ ቤቶች መርሆችና ጥበቃ

የባህላዊ ፍርድ ቤቶች መቋቋም፣ እውቅና አሰጣጥና አሰራር በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-

1. በባለጉዳዮች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እና አማራጭ ስለመሆናቸው፤
   ሀ) የባህላዊ ፍርድ ቤቶች እንደ አማራጭ የግጭት እና አለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች ሆነው ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ጎን ለጎን ያገለግላል፤

ለ) ማንም ሰው ካለፈቃዱ በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ሊዳኝ አይችልም፡፡

2. ባህላዊ ሥርዓቱ ላይ ጉዳት ያለማድረስ፤ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ አስገዳጅ መርሆች እንደ ተጠበቁ ሆነው የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ እና እውቅና መስጫ ሕጎች የባህላዊ ተቋማትን እና አሰራሮችን ተዓማኒነት እና ባህላዊ ዕሴቶችን ባስጠበቀ መልኩ መመስረት ይኖርባቸዋል፡፡

3. የሠብዓዊ መብት ጥበቃዎች፡-

ሀ) በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚፈጸሙ ሥነ-ሥርዓቶች በሙሉ የባለጉዳይ ወገኖችን ሠብዓዊ መብት ያከበሩ መሆን አለባቸው፤

ለ) ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሰዎችን ማህበራዊ ሁኔታ፣ ዘር፣ ብሔር፣ ዜግነት፣ ማህበራዊ መገኛ፣ የቆዳ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ ህሳቤ፣ ሀብት፣ ትውልድ፣ አካል ጉዳት ወይም ሌላ ደረጃ ላይ ከተመሰረተ አድልዕዎ ነፃ በሆነ መልኩ መዳኘት እና አገልግሎት መስጠት አለባቸው፤

ሐ) ሴቶች እና ወንዶች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች በእኩልነት መስተናገድ አለባቸው፤

መ) ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የህፃናትን የቀደምትነት ጥቅም የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው፤

ሠ) ባህላዊ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ባለጉዳይ ወገኖች አስተርጓሚ ይዘው የመቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነዉ፤

ረ) በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚተላለፍ የቅጣት ውሳኔዎች አካላዊ ቅጣትን ጨምሮ ኢሠብዓዊ፣ ጭካኔን የተሞላ ወይም ሰዉ የሚያዋርድና ክብረ-ነክ መሆን የለባቸውም፤

ሰ) በፍርድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት ወቅት በባህላዊ ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ የሠብዓዊ መብት ጥሰት ይግባኝ የመጠየቂያ በቂ ምክንያት መሆን ይችላል፡፡

4. ተደራሽነት

ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ማህበረሰቡ በሚገኝበት እና አገልግልቱ ተደራሽ በሚሆንበት አግባብ እንዲደራጁ እና እውቅና እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት
## የባህል ፍርድ ቤቶች መቋቋም፣ እዉቅና ስለመስጠት፣
## አደረጃጀት፣ መሰረዝና ሥልጣንና ተግባር፡፡

### አንቀጽ 7
### የባህል ፍርድ ቤቶችን ማቋቋም እና አዉቅና አሰጣጥ

1. የባህል ሕግን መሠረት አድርጎ የሚሰሩ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የባህል ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. የባህል ሕግን መሠረት አድርጎ አለመግባባትን የሚፈቱ የባህል ፍርድ ቤት አደረጃጀት ያላቸው የማህበረሰብ ተቋማት ዕውቅና ሊሰጣቸው የሚችል ሆኖ የባህል ፍርድ ቤቶች እውቅና አሰጣጥ እንደሚከተለዉ ይሆናል፡-

   ሀ) የባህል ተቋማት እንደየ ባህላዊ ፍርድ ቤት እውቅና ለማግኘት በፍትህ ቢሮ መመዝገብ ይኖርበታል፤

   ለ) አለመግባባቶችና ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስችል አደረጃጀት ያለዉ መሆኑ፤

   ሐ) እዉቅና ለማግኘት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ጥያቄ ስለመቅረቡ መረጋገጡ፤

   መ) በዚህ አዋጅ የተቀመጡትና ዓላማዎችና መርሆዎችን የተከተለ መሆኑ፤

3. የምዝገባና የእውቅና አሰጣጥ ዝርዝር መስፈርቶች በተመለከተ ዝርዝር በደንብና በመመሪያ ይወሰናል፤
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት አለመመዝገባቸው በተለመደው የባህላዊ የአሰራር ሁኔታ ከመስራት አይገድባቸውም፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም በባህል ሕግ መሠረት አለመግባባትን የሚፈታ ማንኛውንም የማህበረሰብ ተቋማት በተለመደዉ ሁኔታ ከመስራት የሚከለክሉ አይሆኑም፡፡

## አንቀጽ 8

## ዕዉቅና የተሰጣቸዉ ባህል ፍርድ ቤቶች እዉቅናዉን ስለመሰረዝ

1. እውቅና ሰጪው አካል ለባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሰጠውን እውቅና ሊሰርዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የባህላዊ ፍርድ ቤቶች እውቅና ሊሰረዝ የሚችው፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መሰረታዊ መርሆዎችንና መስፈርቶች ሲጣሱ፤ ወይም
   ለ) የባህል ፍርድ ቤቱ እውቅናው ወይም ምዝገባው ለመቀጠል የማይፈልግ መሆኑን በፅሁፍ ሲገለጽ ነዉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሰረት የባህላዊ ፍርድ ቤት እዉቅና ሲሰረዝ የተሰረዘበትን ምክንያት በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም እውቅናው የተሰረዘ የባህል ተቋም በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን በማሟላት እንደ ባህሊዊ ፍርድ ቤት በድጋሚ ከመመዝገብ አያግድም፡፡

## አንቀጽ 9

## የባህል ፍርድ ቤት አደረጃጀት

1. የባህል ፍርድ ቤት የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-
   ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ  የባህል ፍርድ ቤት እና
   ለ) እንዳስፈላጊነቱ ይግባኝ ሰሚ የባህል ፍርድ ቤት ይኖሩታል፡፡
2. የመጀመሪያ ደረጃ ባህል ፍርድ ቤት በቀበሌ ደረጃ መስተዳድሮች ላይ ሊቋቋም ይችላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ለሁለትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ቀበሌዎች አንድ የባህል ፍርድ ቤት ሊቋቋም ይችላል፤
4. በዚህ አንቀጽ 3 ስር የተደነገገዉ ቢኖርም በአንድ ቀበሌ አስተዳደር ዉስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋ የሚናገሩ ብሄረሰቦች ካሉ በባህላቸዉ እንዲስተናገዱ በሚያመች

መልኩ በልዩ ሁኔታ በአንድ ቀበሌ ዉስጥ ሁለት የባህላዊ ፍርድ ቤት ሊቋቋም ይችላል፤

5. ይግባኝ ሰሚ የባህል ፍርድ ቤት በወረዳ ደረጃ እና እንደ አስፈላጊነቱ በከተማ መስተደድሮች ላይ የሚቋቋም ሆኖ፡-
   ሀ) የይግባኝ ሥርዓት ያላቸው ባህላዊ ሥርዓቶች በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ደረጃ እውቅና አግኝተው እንዲደራጁ ይደረጋል፤
   ለ) የባህላዊ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በባህል ሕጉ መሰረት የተደራጀ የመጀመሪያ ደረጃ ባህላዊ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የመጨረሻ ይግባኝ የማየት ሥልጣን አለው፤
   ሐ) መደበኛ የወረዳ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ባህላዊ ፍርድ ቤት ወይም ከይግባኝ ሰሚ ባህላዊ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ከመሰረታዊ የሠብአዊ መብት መርሆችና በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ በሕግ ሥርዓቶች አንፃር በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡
6. በባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌዎች በልዩ ሁኔታ የሚወሰን ቢሆንም፡-
   ሀ) የይግባኝ ሰሚ የባህል ፍርድ ቤት መቀመጫ የወረዳው አስተዳደር ማዕከል ከተማ ይሆናል፤
   ለ) የከተማ መስተዳደር የባህል ፍርድ ቤት መቀመጫ በከተማው አስተዳደር ማዕከል እና
   ሐ) የመጀመሪያ ደረጃ የባህል ፍርድ ቤት መቀመጫ በቀበሌው አስተዳደር ማዕከል ይሆናል፤
7. የመጀመሪያ ደረጃና የይግባኝ ሰሚ የባህል ፍርድ ቤት የሚከተሉት አካላት ይኖራቸዋል፡-
   ሀ) የፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ሸማግሌ እና
   ለ) የፍርድ ቤቱ ሸማግሌዎች፡፡
8. የባህል ፍርድ ቤት የፍርድ ቤቱ ጸኃፊና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፤
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ከአንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 8 እና በአዋጁ ሌሎች አንቀፆች የተደነገገ ቢኖርም በአከባቢው ባህል ሕግ መሠረት ለሚታወቅ የባህል ፍርድ ቤት አደረጃጀት አሰያየምና ቋሚ መቀመጫ እውቅና ሊሰጠው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 10

## የባህል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

1. የመጀመሪያ ደረጃ የባህል ፍርድ ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ተቀብሎ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡-
   ሀ) የቤተሰብና ግላዊ ጉዳይ፤
   ለ) በአዋጅ በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሰረት በሰጡት ዉሳኔ እና በሚመለከታቸዉ ጉዳይ ላይ ማስረጃ የመስጠት፤
   ሐ) በግል አቤቱታ የሚቀረቡ የወንጀል ጉዳዮችን እና የደንብ መተላለፍ ድርጊቶች
   መ) በባለ ጉዳዮች ስምምነት መሰረት ማንኛዉንም የፍትሃብሔር ጉዳዮችን የማየት፤
   ሠ) በሌሎች ሕጎች ላይ በግልጽ ተለይተው የማየት እና የመወሰን ሥልጣን በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ አይቶ የመወሰን ሥልጣን አላቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባህል ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት ከሚከተሉት መስፈርቶች መካከል ቢያንስ አንዱ መሟላት አለበት፡፡
   ሀ) ከተከራካሪ ወገኖች ቢያንስ አንዱ የባህል ፍርድ ቤት ሥልጣን ወሰን በሚገኝ ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ ወይም ተወላጅ ከሆነ ወይም
   ለ) ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቋሚ ንብረት የባህል ፍርድ ቤቱ የሥልጣን ወሰን በሆነው ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ወይም
   ሐ) የጉዳዩ መነሻ በባህል ፍርድ ቤት የሥልጣን ወሰን ውስጥ የተጀመረ ወይም ፍፃሜ ያገኘ ከሆነ ነው፡፡
3. ባሕላዊ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ሥልጣን ይኖረዋል፡-
   ሀ) በክርክሩ ድርሻ ያላቸውን ወገኖች ማስታረቅ፤
   ለ) የሚከፈል ካሳን መወሰን፤
   ሐ) ወጪና ኪሰራን ማስከፈል፡፡
4. ሥልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት የቀረበለት ጉዳይ በባህል ፍርድ ቤት እልባት ማግኘት አለበት ብሎ ካመነ ወይም የሚያዝ ሕግ ሲኖር በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ጉዳዩን አይቶ መፍትሄ እንዲሰጥ ለባህል ፍርድ ቤት መምራት ይችላል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የባሕል ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የአስማሚነት እና የማስታረቅ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡-
   ሀ) ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ለሽምግልና ወይም ለግልግል የሚላኩለቸው ጉዳዮች፤
   ለ) በወንጀል ጉዳዮች ላይ መደበኛ የወንጀል የሕግ ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጎጅን እና በዳይን ሊያስታርቁ ወይም ሊያሸማግሉ ይችላሉ፤
   ሐ) የማስታረቅ ሂደት ባላጉዳዮች ፈቃዳቸውን ሳይሰጡ ሊጀመር አይችልም፡፡
6. የእርቅ ሂደት ላይ የተገለጹ ማናቸውም ጉዳዮች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን ጥፋተኝነት ለማስረዳት በማስረጃነት መቅረብ አይችልም፤
7. የባህል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመጀመርያ ደረጃ ባህል ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርበውን ቅሬታ የማየት ሥልጠን እና እንደአስፈላጊነቱ በራሱ የሚያያቸዉ ጉዳዮችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤
8. ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች በጥፋተኞች ወይም ወንጀለኞች እና በተበዳዮች ወይም ሕዝብ መካከል የሚኖር የይቅርታ ሥነ-ሥርዓት ማመቻቸት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤
9. ይርጋን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ የጊዜ ገደቦች ወይም የይርጋ ድንጋጌዎች የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## <u>አንቀጽ 11</u>

## <u>የባህላዊ ፍርድ ቤት ዉሳኔ አፈጻጸም</u>

1. በዚህ አዋጅ መሰረት እውቅና በተሰጠው ባህላዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ በይግባኝ እስካልታገደ ወይም እስካልተሻረ ድረስ በባለጉዳዮች ላይ የፀና ይሆናል፤
2. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚያስተላልፉትን ውሳኔ ለባለጉዳዮች በጽሁፍ መስጠት አለባቸው፤

3. ውሳኔውን ለመቀበልና ለመፈፀም እምቢተኛ የሆነን ባለጉዳይ ባህላዊ ፍርድ ቤቱ በባህል ሕጉ መሰረት አስገዳጅ እርምጃዎችን በመውሰድ ሊያስፈፅም ይችላል፤
4. ባለዕዳ የሆነ ባለጉዳይ የባህላዊ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለመፈፀም እምቢተኛ በሆነ ጊዜ እና ውሳኔው በመንግስታዊ ወይም የግል ተቋማት በኩል ማስፈፀም የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ የባህላዊ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ጠቅሶ ውሳኔውን እንዲያስፈፅምለት በተመዘገበበት አካባቢ ለሚገኝ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርድ ባለመብት በኩል ሊያስተላልፍ ይችላል፤
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ጉዳዩ የቀረበበት ወረዳ ፍርድ ቤት የባህላዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረን መሆኑን አረጋግጦ ውሳኔውን በመደበኛ የፍርድ አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት መሰረት ያስፈፅማል::

## አንቀጽ 12

## የዳኝነት ሥልጣን አለመኖር

ባህላዊ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመዳኘት ስልጣን አይኖራቸውም፡-

1. ባህላዊ ፍርድ ቤቶች የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ አይችሉም ፤
2. በዐቃቤያነ-ሕግ ክስ አቅራቢነት በሚታዩ ወይም ተጎጂ ግለሰብ የሌላባቸው የወንጀል ጉዳዮች፤
3. በግል አቤቱታ በሚታዩ ወንጀል ወይም የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በባህላዊ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑ ከታወቀ በፖሊስ የተጀመረ ምርመራ መዝገብ ይቋረጣል፤
4. መንግስትንና የመንግስት ተቋማትን የሚመለከቱ፣ በክስ አቅራቢነት ብቻ የሚሰሙ ወንጀሎች፤
5. ለመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 5 ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት መሰረት መደበኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በባህላዊ ፍርድ ቤት ታይቶ ዉሳኔ እንዲሰጥ ብሎ መዝገቡን ወደ ባህላዊ ፍርድ ቤት ከመራዉ የሚቻል ይሆናል፡፡
7. የክልል ወይም የፌዴራል መንግስትን በቀጥታ በሚመለከቱ ጉዳዮችን፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት መቋቋም፣

## አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 13

### ስለ መቋቋም

1. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች እውቅና አሰጣጥና አስተዳደርን የሚተገበር ክልል የባህል ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤት (*ከዚህ በኋላ **"የባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት"***) እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. የተቋቋሙት የባህላዊ ፍርድ ቤቶች አስተዳደር ምክር ቤቶች የጋራ ጉባኤ ሊያካሂዱ ይችላሉ፤
3. የባህል ፍርድ ቤት ጽህፈት ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል፤
4. የባህል ፍርድ ቤት ምክር ቤቱ ተጠሪነት ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል።

### አንቀጽ 14

### የባህል ፍርድ ቤት ምክር ቤት አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት……………………………ሰብሳቢ
2. የፍትህ ቢሮ ኃላፊ …………………………………………….ም/ሰብሳቢ
3. የብሄረሰብ ምክር ቤቶች ዋና አፈ-ጉባኤዎች…………………አባል
4. የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ……………… …………አባል፤
5. የሠላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ……………………… …………አባል፤
6. የባህልና ቱሪዚም ቢሮ ኃላፊ…………………………… …………አባል፤
7. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር …………………………… …………አባል፤
8. የክልሉ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር…………………………… አባል፤

9. የክልሉ ጠበቆች ማህበር ፕሬዚዳንት....................አባል ናቸው፡፡

## አንቀጽ 15

## የባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

ባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት የሚከተለት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአዋጁን አጠቃላይ አፈፃፀም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
2. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች የሚቋቋሙበትን፣ እውቅና የሚያገኙበትን፣ የሚስፋፉበትን እና የሚደራጁበትን መንገድ ያመቻቻል፤
3. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች በአገልግሎት አሰጣጥና በአፈፃፀም የሚገጥማቸውን ችግር በጽህፈት ቤቱ በኩል እየተከታተለ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
4. የባህላዊ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ በተመለከተዉ መሰረት ሥራቸዉን ማከናወናቸዉን በጽህፈት ቤቱ አማካኝነት በየጊዜዉ ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
5. የባህላዊ ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች በየጊዜዉ ሥልጣናቸዉን እንዲያገኙ ያደርጋል፤
6. ከክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር ይተባበራል፤ በየዓመቱም የጋራ ምክክር ያካሂዳል፤
7. የባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤቱ የራሱን የውስጥ የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

## አንቀጽ 16

## የባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት ጽህፈት ቤት

1. የባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት ጽህፈት ቤት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የሚደራጅ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጽህፈት ቤቱ አስፈላጊ በጀትና

የሰው ኃይል ያስመድባል፣ይመድባል፤

3. ጽህፈት ቤቱ ለባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤት ጽህፈት ቤት አገልግሎት ይሰጣል፤ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ይመራል፤
4. የባህላዊ ፍርድ ቤት ምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈፅማል፣ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ምርጫና ሂደቱ

### አንቀጽ 17

### የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች የምርጫ መስፈርት

1. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ሆኖ የሚመረጥ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡-
   ሀ) የባህል ፍርድ ቤቱ የሚሰራበትን አካባቢና ብሄረሰብ የባህል ሕግ እና ዕሴቶችን የሚያውቅና የሚያከብር፤
   ለ) በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ዕርቅ የማውረድ ብቃትና ልምድ ያለው፤
   ሐ) የባህል ፍርድ ቤቱ የሚሰራበትን አካባቢና የብሄረሰቡን ቋንቋ በሚገባ የሚችል፤
   መ) የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ሆኖ ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፤
   ሠ) የማንኛዉም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፤
   ረ) የአዕምሮ ጤና እክል ወይም ግዴታውን ለመወጣት የማያስችል የአካል ጉድለት ወይም የጤና ችግር የሌለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተቀመጠዉ መስፈርት የተጠበቀ ሆኖ የባህላዊ ፍርድ ቤት የሽማግሌዎች ምርጫ የሴቶችን ተዋጽዖ ያረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

### አንቀጽ 18

### የምርጫ ሂደት

1. መደበኛ የወረዳ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ባህል፣ቱሪዝምና ስፖርት ጽህፈት ቤት በጋራ የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎችን ምርጫ የሚያስተባብርና የሚመራ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

2. ኮሚቴው የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎችን ለማስመረጥ የቀበሌው አስተዳዳሪ ነዋሪዎችን ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል፤
3. ኮሚቴው የዕጩዎችን ጥቆማ ሲሰጥ በቀበሌና በአከባቢዉ እርቅ በማዉረድ የታወቁ እና ለአከባቢዉ ሠላም ተቆርቋሪ የሆኑ የአከባቢ ሽማግሌችን፣ የአከባቢዉ የጎሳ አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎች እንዲካተቱ ማድረግ አለበት፤
4. ከተጠቆሙ ግለሰቦች መስፈርት የማያሟላ መኖሩ ከተገለጸ ኮሚቴው እንደአስፈላጊነቱ ማጣራት ካደረገ በኋላ ሌሎች ግለሰቦች በዕጩነት እንዲጠቆሙ ያደርጋል፤
5. የድምጽ አሰጣጡ በአካባቢው ባህል መሠረት የሚደረግ ሲሆን ኮሚቴው ከፍተኛ ድምጽ ያገኙ እና አስፈላጊ መስፈርቶችን ያሟሉትን ያስመርጣል፤ የተመረጡ የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ከመካከላቸው ሰብሳቢ ይመርጣሉ፤
6. እንዳስፈላጊነቱ የይግባኝ ሰሚ የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ተመሳሳይ ሂደትን በመከተል የሚመረጡ ሲሆን በባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ጉባዔ የሚመረጡ ይሆናል፤
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው ቢኖርም የሽማግሌዎችን ምርጫ ለማካሄድ የሚረዳ የባህል ሕግ በሚኖርበት ጊዜ ምርጫው በባህል ሕጉ መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 19

## የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ቃለ መኃላ

ለባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌነት የተመረጡ ሽማግሌዎች የምርጫ ውጤት ከታወቀ በኋላ የአካባቢው ባህል በሚፈቅደው መሠረት ታዋቂ ሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት ቃለ-መኃላ እንዲፈጽሙ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 20

## የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች የሥራ ዘመን

1. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ የሥራ ዘመን የክልሉ ብሄረሰቦች ባህል መሰረት በቀጣይ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ ቢኖርም በወረዳ ፍርድ ቤት እና የባህል፣ቱሪዝምና ስፖርት ጽህፈት ቤት በጋራ የሚቋቋመው ኮሚቴ የአካባቢ

ነዋሪዎችን ስብሰባ በመጥራት እንዲሁም የባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌዎችን ጉባዔ በመጥራት በባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌዎች ሥነ-ምግባርና ብቃት ባላቸው ላይ ሀሳብ እንዲሰጡና የስራ ዘመናቸዉን ሊያራዝም ይችላል፤

3. በብቃትና በሥነ-ምግባር ጉድለት ቅሬታ የቀረበበት የባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌ በአካባቢው ባህል መሠረት ሥራውን ለመቀጠል የሚያስችል የድጋፍ ድምፅ ካላገኘ ከስራው በኮሚቴዉ ይሰናበታል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌ የብቃት ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለት ያለው እንደሆነ ጥቆማ ወይም ቅሬታ ሊቀርብበት ይችላል፤
5. የሚቀርበውንም ቅሬታ መሰረት የአካባቢውን ነዋሪ ስብሰባ በመጥራት አጣርቶ ከተረጋገጠበት በየትኛውም ጊዜ ከኃላፊነቱ ማንሳት ይቻላል።

## አንቀጽ 21

## ከሥነ-ምግባር እና ብቃት ማጣት ምክንያት ውጭ የባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌ ከስራው የሚነሳበት አግባብ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌ በሚከተሉት ምክንያቶች ከስራው ሊነሳ ይችላል፡-

1. በፍላጎቱ፤
2. በሞት፣ በአካል ጉዳት ወይም ሥራውን መቀጠል በማያስችሉ ሌሎች የጤና እክሎች፤
3. መኖሪያ አድራሻን በመቀየሩ ምክንያት ሥራውን መቀጠል ካልቻለ፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ስር የተዘረዘሩት የባህል ፍርድ ቤት ሸማግሌዎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ያላሟላ ከሆነ ወይም ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፡፡

## አንቀጽ 22

## ሥራ መልቀቅን ስለማሳወቅ እና የማሟያ ምርጫ

1. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሥራውን መልቀቅ ከፈለገ አንድ ወር አስቀድሞ ለባህል ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ሽማግሌ ማሳወቅ አለበት፤
2. የባህል ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ሽማግሌ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ምክንያት ስራ ለመልቀቅ ከፈለገ ለወረዳ ፍርድ ቤት ማሳወቅ አለበት፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ቁጥር ከጎደለ የባህል ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ሽማግሌ ለወረዳ ፍርድ ቤት ማሳወቅ አለበት፤
4. የወረዳ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ባህል፣ቱሪዝም ስፖርት በጋራ የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌን ለማስመረጥ በተቋቋመው ኮሚቴ መሠረት በጎደለው ሽማግሌ ቦታ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 የተገለፀውን ሥነ-ሥርዓት በመከተል ምትክ ሽማግሌ እንዲመረጥ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 23
## የሥራ ነፃነት

1. የባህል ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ ከኃይማኖት ከግል አመለካከት እና ከማንኛውም አካል ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በባህል ሕግና በእያንዳንዱ ብሄረሰብ እሴቶች ላይ ብቻ ተመስርተው በፍትህ እና በገለልተኛነት ስራቸውን ይመራሉ፤
2. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ለሕሊናቸው፣ በባህል ሕግና በማህበረሰቡ እሴቶች ብቻ የሚመሩ ይሆናል፤
3. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ሥልጣናቸው በሆነ ጉዳይ ላይ ወይም በቅን ልቦና ሥልጣን እንዳላቸው አስበው በባህል ሕግ መሠረት በሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ ምክንያት የወንጀል እና የፍትሐብሔር ተጠያቂነት የለባቸውም፡፡

## አንቀጽ 24
## የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ግዴታዎች

ማንኛውም የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. ሥራው የሚፈልገውን ሥነ-ምግባር ማክበር፤

2. ያታን፣ ኃይማኖትን፣ ጎሳን፣ ዕድሜን የኢኮኖሚ ሁኔታን፣ የፖሊቲካ አመለካከትንና ማንኛውንም ሁኔታ መሠረት በማድረግ አድልዎ ከመፈፀም መቆጠብ፤
3. በጥቅም ከመስራት ነፃ መሆን፤
4. ምሳሌ መሆን የሚችል፣ መልካም ፀባይ እና የፍርድ ቤቱን መልካም ሥም መገንባት የሚችል የግል ሕይወት ያለው፤
5. ሚስጢር መጠበቅ፤
6. የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል አለመሆን፤
7. ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ማንኛውንም ውሳኔ የራሱ አድርጎ መውሰድ፤
8. የግል ጥቅሙ ያለበት ጉዳይ ከቀረበ ከባህል ዳኝነት ችሎት እራሱን ማንሳት፡፡

## አንቀጽ 25

## የባህል ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ስራ እና ኃላፊነት

የባህል ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ሽማግሌ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 ስር ከተዘረዘሩት የሽማግሌዎች ግዴታ በተጨማሪ የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. የባህል ዳኝነት ችሎት የሚቀመጡበት ቀን ወስኖ ሽማግሌዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ማሳወቅ፤
2. የባህል ፍርድ ቤቱን የስራ ክንውን ሪፖርት ለሚመለከተው አካል መላክ፤
3. የባለጉዳዮችን እና ምስክሮችን ቃለ-መኃላ ማስፈፀም ወይም እንዲፈፅሙ ማድረግ፡፡

## አንቀጽ 26

## የባህል ፍርድ ቤት ጸኃፊ

1. የባህል ፍርድ ቤት አንድ ጸሐፊ ይኖረዋል፤
2. የባህል ፍርድ ቤት ጸሐፊ ሆኖ የሚመደብ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሀ"፣ "ለ" እና "ሐ" ስር የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤ ተጨማሪ መስፈርቶች ቀጣይ በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤
3. የባህል ፍርድ ቤት ጸሐፊን አወዳድሮ የሚመድበው የወረዳ ፍርድ ቤት ይሆናል፤ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 27

## የባህል ፍርድ ቤት ጸኃፊ ሥራና ግዴታ

የባህል ፍርድ ቤት ጸሐፊ የሚከተሉት ሥራዎች ይኖሩታል፡-

1. በባህል ዳኝነት ችሎት ላይ በመገኘት በቃል የሚሰጡ አቤቱታና መልስ፣ የቃል ክርክር የምስክሮች ቃል፣ የሚሰጡ ውሳኔዎች እና ትዕዛዞችን መፃፍ፤
2. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች በሚሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ፊርማቸውን ማስፈረም፤
3. ክስ የሚሰማበት የመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ በመያዝ ለከሳሽ ማሳወቅ፤
4. የሚቀርቡትን ማስረጃዎች መቀበልና በስርዓት መያዝ መዝገብ ማደራጀት እና ቁጥር መስጠት፤
5. በባህል ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ሲታዘዝ የውሳኔ ግልባጭ መስጠት፤
6. የስራ ክንውን ሪፖርትን በማደራጀት ለባህል ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ያቀርባል፤ እንዲሁም ለወረዳ ፍርድ ቤት በወቅቱ ይልካል፡፡

## ክፍል ስድስት

## በባህላዊ ፍርድ ቤት ሥራ ቋንቋ፣ ተግባራዊ የሚደረግ ሕግ እና የጉዳዮች አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

## አንቀጽ 28

## የሥራ ቋንቋ

1. የባህል ፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ እንደየ አከባቢዉ የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች ቋንቋ ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ዉስጥ የሚኖሩ ማንኛዉም ብሄረሰቦች በራሳቸዉ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፤
3. የአካባቢዉን ቋንቋ የማይችል ተካራካሪ ወገን ወይም ሰዉ ካጋጠመ የባህል ፍርድ ቤቱ ከአከባቢው ማህበረሰብ ቋንቋውን መተርጎም የሚችል ሰው እንዲያግዝ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 29

## ፈቃድን ስለመስጠትና ፈቃደኝነት የሚረጋገጥበት ሁኔታ

1. ለባህል ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ያቀረበ ሰው በባህል ፍርድ ቤቱ ለመስተናገድ ፈቃዱን እንደሰጠ ይቆጠራል፤
2. ፈቃድ ከማናቸውም ፍራቻ፣ ተጽዕኖ ወይም ዛቻ ነጻ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ መገለጽ ይኖርበታል፤
3. ፈቃድ በቃል፣ በምልክት ቋንቋ ወይም በጽሁፍ ሊገለጽ ይችላል፣ ሆኖም በባህላዊ ፍርድ ቤት መቅረብ ብቻውን ፈቃድ እንደ መስጠት አይቆጠርም፤
4. ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ከቀረበ በኋላ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ከመደረጉ በፊት ጉዳዩ በባህል ፍርድ ቤት እንዲታይ ካልተቃወመ በስተቀር በባህላዊ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ እንደሰጠ ይቆጠራል፤
5. ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ጉዳዩ በባህል ፍርድ ቤት እንዲታይ ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ ማንሳት አይችልም፤
6. ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ እና በፍርድ ክልከላ ያለበት ሰው ፈቃድ የሚሰጠው በሞግዚቱ አማካኝነት መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 30

## ሥራ ላይ የሚውል ሕግ

1. የባህል ፍርድ ቤት ሥራ ላይ የሚያውለው ሕግ የአካባቢ ብሄረሰብ የባሕል ሕጎችን መሰረት በማድረግ ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የባህል ሕጉ ከሚከተሉት ጉድለቶች ውስጥ አንዱን ቢኖረው ተፈፃሚነት አይኖረውም፡-

   ሀ) የተፈጥሮ ፍትህን የሚቃረን ከሆነ ወይም

   ለ) እኩልነት የሚቃረን ከሆነ ወይም

   ሐ) የማህበረሰቡን ሞራልና ግብረ-ገብ የማያከብር ከሆነ ወይም

መ) በሰዎች መካከል በእምነት፣ በጾታ፣ በመልክ፣ በእድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ በብሔር፣ በፖለቲካ፣ አመለካከት፣ በሃብት ወይም በሌላ ምክንያት አድልዎን የሚፈጥር ከሆነ ወይም

ሠ) ሠብዓዊ መብትን የሚፃረር ከሆነ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባህል ፍርድ ቤቶች ሴቶችን፣ ህፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የህበረተሰብ ክፍሎችን የሚያበረታቱ የባሕል ሕጎችንና አሰራሮችን ሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ።

## አንቀጽ 31

## የጉዳይ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

1. ጉዳዩ በባህል ፍርድ ቤት እንዲታይለት የሚፈልግ ሰው የባህል ፍርድ ቤቱን ጸሐፊ በማናገር ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ያስይዛል፤
2. የባህል ፍርድ ቤት ጉዳይን መሰማት ከመጀመሩ በፊት በባህል ሕጉ መሠረት መገኘት ያለባቸው ሽማግሌዎች መሟላት አለባቸዉ፤
3. ጉዳዩ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን ከሳሹ የባህል ዳኝነት ችሎት ፊት ቀርቦ ጉዳዩን ማቅረብ አለበት፤
4. የባህል ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ ወይም አቤቱታ ለማየት ሥልጣን የሌለው ከሆነ ወይም ከሳሽ በባህል ሕጉ መሠረት ከጉዳዩ ጥቅም የሌለው ከሆነ ወይም የክስ ምክንያት የለውም ብሎ ያመነ እንደ ሆነ ተከሳሽን መጥራት ሳያስፈልግ ጉዳዩን ዘግቶ ከሳሽን ማሰናበት ይችላል፤
5. ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ሰው በባህል ፍርድ ቤት ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ሽማግሌዎች ባመኑበት ሰው አማካኝነት መጥሪያ እንዲደርሰው ይደረጋል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት መጥሪያ ደርሶት የቀረ ሰው ለሁለተኛ ጊዜ ጥሪ ይደረግለታል፤
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ስር በተደነገገው መሠረት ጥሪ የተደረገለት ሰው መቅረብ ካልቻለ በአከባቢው የባህል ሕግ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፤

8. ተከሳሽ በጥሪው መሠረት በቀነ ቀጠሮ ከቀረበ የቀረበበት ክስ ወይም አቤቱታ በባህል ዳኝነት ችሎት ሊገለፅለት ይገባል፤
9. ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ ከሰማ በኋላ በባህል ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ እንዲታይለት ፈቃደኝነቱ ከተረጋገጠ የባህል ፍርድ ቤቱ የቀረበበት ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ ማዘዝ ወይም ሌላ እርምጃ መውሰድ ይችላል፤
10. ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ ያመነ እንደ ሆነ የባህል ፍርድ ቤቱ በሚሰራበት አከባቢ ባለው የባህል ሕግ መሠረት ውሳኔ ወይም አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፤
11. ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ የካደ እንደ ሆነ የባህል ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ መንገድ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት ይችላል፤
12. ባለመግባባት ውስጥ ያሉ ወገኖች የጉዳዩ መሰማት ሂደት ተጀምሮ ከቀጠለ በኋላ ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ፣ የባህል ፍርድ ቤቱ በባህል ሕጉ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል፤
13. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 11 የተደነገገው ቢኖርም የባህል ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ሲመለከት የባህል ፍርድ ቤቱ የሚሰራበት አከባቢ ያለውን ሌላ የባህል ሥነ-ሥርዓት ሕግን መከተል ይችላል፤
14. ከሳሽ የሚያቀርበው ማንኛውም ክስ ወይም አቤቱታ ወይም ተከሳሽ የሚያቀርበው ማንኛውም መልስ በአቅራቢው ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ በጽሑፍ ወይም በቃል ሊሆን ይችላል፤
15. በባህል ፍርድ ቤት የሚታየው ጉዳይ ላይ ማንኛውም ወገን በሕግ ጠበቃ ክርክር ማቅረብ አይችልም፤
16. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራካሪ ወገኖች በቤተሰብ አባል ወይም የባህል ፍርድ ቤቱ የሚሰራበት አከባቢ ባለው የባህል ሕግ መሠረት ለሚፈቀድለት ሰው መወከል ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 32

## ምስክር መስማት

1. የባህል ፍርድ ቤት የያዘውን ጉዳይ ያብራራል ብሎ ያመነን ወይም በባለጉዳዮች የተጠቆመን ማንኛውንም ሰው እንዲቀርብ ጥሪ ያደርግለታል፤

2. ምስክር እንዲሆን በባህል ፍርድ ቤት ጥሪ የደረሰው ሰው በቂ ባልሆነ ምክንያት ለመቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ የባህል ፍርድ ቤቱ በባህል ሕግ መሰረት እንዲቀርብ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ወይም በቀበሌ አስተዳደር በኩል ቁጥጥር ስር ውሎ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 33

## የምስክሮች ቃለ-መኃላ አፈጻጸም

1. የባህል ፍርድ ቤት ክስ አቤቱታ መልስ እንዲሁም ምስክር ከመስማቱ በፊት ባለጉዳዮች ወይም ምስክሮች የባህል ፍርድ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ባህል መሠረት ወይም በግለሰቡ እምነት መሠረት ቃለ-መኃላ እንዲፈፅም ያደርጋል፤
2. ማንኛውም ሰው ሌላ ሰው ተለይቶ በአቤቱታ ውስጥ የተገለፀን ድርጊት መፈጸሙን ወይም አለመፈፀሙን መኃላ ፈፅሞ እንዲታመንለት ለባህል ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤
3. የባህል ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡ ካደረገ በኂላ በአከባቢው ባህል መሠረት መኃላ ፈፅመው እንዲተማመኑ ያደርጋል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ማመልከቻ ቀርቦበት ፈጽሞ ለመተማመን ፍላጎት የሌለው ሰው የተጠረጠረበትን ድርጊት እንደፈጸመ ተቆጥሮ የባህል ፍርድ ቤት አስፈላጊውን ትእዛዝና ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 34

## በአካል ተገኝቶ ጉዳዮችን ማየት

የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች የመሬት ድንበር አለመግባባት፣ በመንገድ የመጠቀም መብት የማግኘት፣ ከወንዝ ውሃ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ እና አስፈላጊ ሆኖ የተገኙ ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ለግጭቱ ምክንያት የሆነ ቦታ ላይ ተገኝቶ ጉዳዩን ማጣራት ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 35

## የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

1. የባህል ፍርድ ቤት የቀረበለት ጉዳይ በባለጉዳዮች እርቅ ስምምነት እንዲያልቅ ጥረት ያደረጋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጉዳዩ በእርቀ ስምምነት ከተጠናቀቀ ችሎቱ የስምምነቱን ይዘት መዝግቦ ተከራካሪዎችን ያሰናብታል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የዕርቅ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ስምምነቱ በባህል ፍርድ ቤቱ እንደተሰጠ ውሳኔ ተቆጥሮ እንዲፈፀም ይደረጋል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ንዑስ እስከ አንቀጽ 3 መሠረት ጉዳዩ በባለጉዳዮች መካከል በሚደረግ የዕርቅ ስምምነት መፍትሄ መስጠት ካልተቻለ የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ጉዳዩ በማጣራት የአከባቢው የባህል ሕግ የሚፈቅደውን አካሄድ በመከተል የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ይሰጣሉ፤
5. ሽማግሌዎች ለሰጡት የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መነሻ ያዳረጉትን የባህል ሕግ እና ምክንያት በግልፅ ለባለጉዳዮች በባህላዊ ዳኝነት ችሎት ላይ ማሳወቅ አለባቸው፤
6. ሽማግሌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በሰጡት የዕርቅ ውሳኔ ላይ ባለጉዳዮች እንዲስማሙ እና የተስማሙበትን እንዲፈፅሙ ለማስማማት ጥረት ያደርጋሉ፤
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ባለጉዳዮቹ ማስማማት ካልተቻለ ለሚመለከተው አካል ቅሬታውን ማቅረብ ለሚፈልግ ወገን የይግባኝ መብት ይጠበቃል፡፡

## አንቀጽ 36
## የእርቅ ውሳኔ አይነት

1. የባህል ፍርድ ቤት ከሚከተሉት የውሳኔ አይነቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ አጣምሮ መስጠት ይችላል፡-
   ሀ) ጥፋተኛ መሆኑን ያረጋገጠን ሰው መምከርና ማስጠንቀቅ፤
   ለ) በባህሉ መሰረት የጉዳት ካሳ መወሰን፣ ንብረት ማስመለስ ወይም የንብረትን ግምት ማስከፈል፣ ከኢኮኖሚ ጉዳት ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ የትኛውንም ጥያቄ ማስከበር፤
   ሐ) የተከሰሰ ወገን አንድን ድርጊት ተመልሶ እንዳይፈፅም ወይም እንዲፈፅም ማድረግ፤

መ) ወጪ እና ኪሳራ መወሰን፤

ሠ) የጉልበት ሥራና ማህበራዊ አገልግሎት እንዲፈጽም መወሰን፤

ረ) የባህል ፍርድ ቤቱ በሚሰራበት አካባቢ ባሉ የባህል ሕጎች ተቀባይነት ያላቸው ሌሎች ውሳኔዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባህል ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የውሳኔ አይነቶች ሲሰጥ በአካባቢው የባህል ሕግ መሰረት በገንዘብ ወይም በዓይነት እንዲፈፀም መወሰን ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 37</u>

## <u>ይግባኝ</u>

1. ከመጀመሪያ ደረጃ ባህል ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን እንደብሄረሰቡ ባህል ለይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤
2. ከይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታው ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከሆነ ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤

   ሀ) የባለጉዳዮቹን የእኩልነት መብት የማያከብርና የሚጥስ የባህል ሕግ ሥራ ላይ ማዋል፤

   ለ) የመሰማት መብት ወይም የቀረበውን ክርክር ለማረጋገጥ በአንድ ወገን የቀረበ ወሳኝ የሆነ ማስረጃን አለመቀበል፤

   ሐ) በሕገ-መንግስት እና አገራችን በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች ውስጥ የተገለፁ ሠብዓዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶችን የሚጥስ የባህል ሕጎች እና አሰራሮችን ሥራ ላይ ማዋል፡፡
3. የባህል ፍርድ ቤት በሚሰጠው የእርቅ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው ከተሰጠ ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ግልባጭ መጠየቅ አለበት፤
4. የባህል ፍርድ ቤት የውሳኔው ግልባጭ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ግልባጭ ለጠየቀው ወገን መስጠት አለበት፤
5. ከባህል ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለበት ሰው ግልባጩን ከወሰደ ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው አካል ማቅረብ አለበት፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እስከ ንዑስ አንቀጽ 5 ስር የተደነገገው ቢኖርም የባህል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ወይም የባህል ይግባኝ ፍርድ ቤት አሳማኝ ምክንያት መቅረቡን ካረጋገጠ ከላይ በተጠቀሰው ቀነ ገደብ ሳይገደብ የውሳኔ ግልባጭ መስጠት ወይም የቀረበውን ቅሬታ ማስተናገድ ይችላሉ፤
7. የይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት የቀረበው ቅሬታ መጣራት እንዳለበት ካመነ መልስ ሰጪ እንዲገኝ መጥሪያ ያደርሰዋል፤
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት መልስ ሰጭ መጥሪያ ደርሶት የቀረ እንደሆነ በሌለበት ጉዳዩን አጣርቶ አስፈላጊውን ውሰኔ ወይም ትእዛዝ ይሰጣል፤
9. የይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት የባህል ሕጎችን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ቅሬታ በማስመልከት የስር ውሰኔ ማሻሻል ወይም ማፅናት ወይም መሻር ወይም አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ያለውን ሕግ እና ፍሬ ነገር በድጋሚ በማጠራት አስፈላጊውን ውሳኔ እና ትእዛዝ መስጠት ይችላል። በዚህ መልኩ የተሰጠ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤
10. የወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከባህላዊ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ቅሬታ በማየት በሕገ-መንግስቱ እና አገራችን በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች ወስጥ የተካተቱ ሠብዓዊ መብቶችን መሠረት በማድረግ አስፈላጊ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ መስጠት ይችላል፤
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ቅሬታ ያለው ሰው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

## አንቀጽ 38

## በባህል ፍርድ ቤት የተሰጠውን የእርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ስለ ማስፈፀም

1. የባህል ፍርድ ቤት ተከሳሽ ወይም ምስክር እንዲቀርብ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ወይም የተጠረጠረ ሰው ቀርቦ በመኃላ እንድታመን የሚሰጠው ትዕዛዝ፣ እንድሁም የቀረበለትን ጉዳይ ካጣራ በኂላ የሚሰጠውን የዕርቅ ውሳኔ በአከባቢ ባህል ሕግ መሠረት ለማስፈፀም ሥልጣን አለው፤
2. በባህል ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለመፈፀም ግዴታ ያለበት ሰው ቀርቦ እንዲፈጸም በባህል ፍርድ ቤቱ ይታዘዛል፤ ፍርድ ቤቱ የታዘዘው ሰው ለመፈፀም ፍላጎት እንደሌለው ከተረዳ፡-

ሀ) ጠርቶ ምክንያቱን ይጠይቃል፤ እንዲፈፅም ያስጠነቅቃል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ሀ" የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ የማይቀበል ከሆነ እንደ ጉዳዩ ተጨባጭ ሁኔታ እና የባህል ፍርድ ቤቱ በሚሰራበት አከባቢ ባለው የባህል ሕግ መሠረት የኢኮኖሚ ወይም የማህበራዊ ማዕቀብ ይጣልበታል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል "ለ" መሠረት በተከሳሽ ላይ የሚጣለው ማዕቀብ እንደተጠበቀ ሆኖ በባህል ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በባህል ሕግ መሠረት ውሳኔውን አስገድዶ ማስፈፀም ወይም በአከባቢዉ ባህላዊ ሥርዓት ተጠቅሞ ወይም የቀበሌ መስተዳደርን በማዘዝ ማስፈፀም ይችላል፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ **"ሀ"** እስከ ፊደል ተራ **"ሐ"** ባሉት የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለማስፈፀም ጥረት ተደርጎ ካልተቻለ የባህል ፍርድ ቤቱ ማስፈጸም ያልቻለበትን ምክንያት በመጥቀስ እንዲያስፈፅም ለወረዳ ፍርድ ቤት ያሳውቃል፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ **"መ"** መሠረት የቀረበለትን የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የወረዳው ፍርድ ቤት በራሱ እንደሰጠ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ወስዶ ያስፈፅማል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጸ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የመጀመሪያ ደረጃ ባህል ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈፅም ሊታዘዝ ይችላል፤
4. የባህል ፍርድ ቤት ካሳን የተመለከቱ ውሳኔዎችን ስያስፈጽም በሚሰራበት አከባቢ ባህል ሕግ መሠረት የሚፈፅም እንዲከፍል ማድረግ እንዲሁም ውሳኔውን የሚያስፈፅምበት ሌላ ሁኔታን ማዘዝ ወይም መወሰን ይችላል፤
5. አንድ ወገን በተሰጠው የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ወደ ይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቆ ከሆነ ጉዳዩ ዕልባት እስኪሰጠው ድረስ አፈፃፀሙ በባህል ሕግ መሠረት ታግዶ እንዲቆይ የባህል ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለ ባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ጉባኤ፣ የስብሰባ ጊዜ እና

## የጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 39

### ባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ጉባኤ፣

1. የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት..............................የጉባኤው ሰብሳቢ፤
2. የወረዳ ባህል እና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ኃላፊ.......... የጉበኤው ምክትል ሰብሳቢ፤
3. የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች...... በጉባኤው አባል ናቸዉ፤
4. የብሄረሰብ ምክር ቤት ባለበት ወረዳዎች ላይ የብሄረሰብ ምክር ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባኤዎች.................................የጉባኤው አባል ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 40

### የጉባኤዉ ስብሰባ ጊዜ

1. የባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ጉባኤ በወረዳ ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ቢኖርም እንደ አስፈላጊነቱ ፕረዝዳንት አስቸኳይ ጉባኤዉ ሊጠራ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 41

### የጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

1. ጉባኤው ከተሳታፊዎች፣ ከጉባኤው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በቀረቡ አጀንዳዎች ላይ ይወያያል፤
2. ጉባኤው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 ላይ በኮሚቴ የተመረጡ የመጀመሪያ ደረጃ ባህላዊ ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚ ባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎችን ምርጫ ያጸድቃል፤
3. የብቃት ማነስ እና የሥነ-ምግባር ጉድለት እንዳለባቸው የተረጋገጡ የባህል ፍርድ ቤት ሽማንግሌዎችን ከሥራ ላይ ያሰናብታል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የክልሉ ብሄረሰብ ምክር ቤት እና የተቋማት ግዴታ

## አንቀጽ 42

## የክልሉ ብሄረሰብ ምክር ቤት ግዴታ

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብና መመሪያ ማዉጣትና ማስፈፀም የተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይሆሩታል፡፡

1. የብሄረሰብ ምክር ቤት ባሉበት ወረዳዎች በባለጉዳዮች ወይም ከሚመለከተው ሌላ አካል በባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ላይ የሚቀርብን የሥነ-ምግባር ቅሬታ በማስተናገድ ኮሚቴ አቋቁሞ ከወረዳ ፍርድ ቤት ጋር ተጣምሮ ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፤
2. የባህል ሕግ እንዲያድግ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ምርምሮችን በማካሄድ ውጤቱ ሥራ ላይ እንዲውል ይሰራል፤
3. የባህል ሕግ ከትውልድ ትውልድ እየተሻገረ እንዲሄድ አስፈላጊውን ሥራ ይሰራል፤
4. የባህል ፍርድ ቤቶች እየተሻሻሉ እንዲሄዱ የሚያስችሉ የትኛውንም ሥራዎች ይሰራል፤
5. ከወረዳ ፍርድ ቤት ጋር በመሆን የባህል ፍርድ ቤቶችን ገቢ ለማሳዳግ የሚረዳ ልዩ ልዩ ድጎማዎችንና ገቢዎች በማፈላለግ ይሰበስባል፡፡
6. የባህል ፍርድ ቤቶች የወጪ ስርዓትን የሚያስተዳድርና ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ያዘጋጃል ህጋዊነቱንም ይቆጣጠራል፡፡

## አንቀጽ 43

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ተዋረድ የፍርድ ቤት መዋቅር ግዴታ

ይህንን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በስሩ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ ውስጥ በተነደገገው መሠረት የባህል ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ አስተዋጽዖ ያደርጋል፤
2. ጉዳዮች በባህል ፍርድ ቤት እልባት እንዲያገኙ ያበረታታል፤
3. የባህል ፍርድ ቤቶችን የሰው ኃይልና ሎጂስቲክ እገዛ ያደርጋል፤

4. ከክልሉ ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ሠብዓዊ መብት የሥነ-ምግባር መርሆዎች እና አስፈላጊ በሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ለባህል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
5. ለክልሉ ምክር ቤት በሚያቀርበው የሥራ ክንውን ሪፖርት ውስጥ የባህል ፍርድ ቤቶች የሥራ ክንውንን ያካትታል፤
6. ግጭቶችን ሲፈቱ ለቆዩ የማህበረሰብ ተቋማት እንደ ባህል ፍርድ ቤት እውቅና ይሰጣል፤ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤
7. በባህል ፍርድ ቤቶች የሚተላለፈውን የቅጣት አፈፃፀም ይከታተላል፤ ጉድለት ባለበት ቦታ አስፈላጊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
8. በባህል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን አፈፃፀም ይከታተላል፤ ድጋፍ እንዲያደርግ ሲጠየቅም ያስፈፅማል፡፡

## አንቀጽ 44

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ቢሮ ግዴታ

1. የዜጎችን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የባህል ሥርዓቱ ሠብዓዊ መብት እና ሕገ-መንግሰቱን ባከበረ መልኩ የባህል ሕጎችን እንፈጸም ያደረጋል፤
2. ባህላዊ የግጭት አወጋገድ ሥርዓቶችን ከዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት ጋር በማቀናጀት የማህበረሰቡን አብሮነት፣ የጋራ ተጠቃሚነትና ዘላቂ ሠላም እንዲረጋገጥ ያደረጋል፡፡

## አንቀጽ 45

## የቀበሌ አስተዳደር ግዴታ

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰነዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር በባህል ፍርድ ቤት ተግባሩን በአገባቡ እንዲፈጸም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1. የባህል ዳኝነት ችሎት ደህንነት ማስጠበቅ፤
2. የባህል ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትእዛዝ መፈፀም ወይም ማስፈፀም፤
3. የባህል ዳኝነት የሚካሄድበትን ቦታ ማመቻቸት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
### አንቀጽ 46
### የገቢ ምንጭ

1. የባህል ፍርድ ቤት የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-
   ሀ) በባህል ፍርድ ቤቱ የሥልጣን ወሰን ውስጥ የአገልግሎት ክፍያ በሕግ አግባብ መሰብሰብ፤
   ለ) መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚሰበሰብ ድጎማ፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም ሁኔታ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 47
### የገቢ አጠቃቀም ሁኔታ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 መሠረት የሚሰበሰብ ገቢ የባህል ፍርድ ቤት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና ለባህል ፍርድ ቤቱ የሥራ መሳሪያዎችን ለማሟላት ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 48
### የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና ለተሰጠው የባህላዊ ፍርድ ቤት ጥያቄ፣ ትእዛዝ እና ውሳኔ አስፈላጊውን ሕጋዊ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

### አንቀጽ 49
### ስለ ተጠያቂነት

ባህላዊ ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ትእዛዝና ውሳኔ በማያከብር ባለጉዳይ ወገን ላይ በባህል ሕጉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ ሆኖም እርምጃው እስርን ማካተት የለበትም፡፡

### አንቀጽ 50
### ደንብና መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን

በክልሉ የሚገኙ የያንዳንዱ ብሄረሰብ ምክር ቤቶች ባህላቸዉን መሰረት በማድረግ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ከክልሉ ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ደንብና መመሪያ የማዉጣት ስልጣን ተሰጧቸዋል፡፡

### አንቀጽ 51
### ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

በዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ የአሰራር ልምድ ወይም ዉሳኔ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

## አንቀጽ 52

## አዋጁ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጸደቀበት የካቲት 11 ቀን/2017 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

አሶሳ

የካቲት 11 ቀን 2017 ዓ.ም

አሻደሊ ሐሰን አልዓጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት